# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልደታ ክፍለ ከተማ

# ትምህርት ፅህፈት ቤት 6ኛ ክፍል ተማሪዎች የመጀመሪያ

# መንፈቀ አመት ሞዴል ፈተና

# አማርኛ ጥር፤2016 ዓ.ም

**የጥያቄ ብዛት፡- 40** **የተፈቀደው ሰዓት፡- 1 ሰዓት**

## አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ ፈተና የአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካቷል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡

በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባቸኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፡፡ በዚህ ወረቀት ላይ ትክክለኛ መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛ መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደውን ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጠቆር አለበት፤ የተጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢያስፈልግ በፊት የተጠቆረውን በደንብ ማጥፋት አለባችሁ፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰአት 1፡00 ሰዓት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን እርሳስ ማስቀመጥና መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ (በፈታኟ) እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ ተቀምጣችሁ መጠበቅ አለባችሁ፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ወይም ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት መልስ መስጫ ወረቀት ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መስራት አይፈቀድም !

መልካም እድል !



LIVEWORKSHEETS

**መመሪያ አንድ፡-** ከተራ ቁጥር 1-7 ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ (ቅንጭብ ጹሁፍ) ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ምንባቡን በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጥ (ምረጪ)፡፡

## ልበ ኩሩነታቸው

…እግራቸውን የሚጎትቱበት አቅም አልነበራቸውም፡፡ እርምጃቸው የሞት ለሆሳስ ይመስላል፡፡ ከወገባቸው ጎበጥ ብለዋል፡፡ ዕድሜ ወይም ህመም አልነበረም፤ ረሀብ ነው፤ ረሀብ እህል በአፋቸው ከዞረ ዛሬ ሶስተኛ ቀናቸው ነው፡፡ ከእዚህ ቀደም አያሌ ቀናትን በዚህ መልክ አሳልፈዋል፡፡ ያኔ የነበራቸው ቆራጥነት ያኔ የነበራቸው የልብ ፅናት በዘመናት እንደተነሳ ለምለም የምድር ገፅ ተሸርሽሮ አልቋል፡፡

እዚህ ድረስ ለመምጣት ከረሀብ ከሆዳቸው ጋር ሁለት ቀንና ሌሊት ተሟግተዋል፡፡ እና ወሰኑ፤ ሞት ዘመናትን በቀረጠፈበት ጥርሱ ሊያላምጣቸው ሲቃረብ እጅ መስጠት አልፈለጉም፡፡ እድሜ ልካቸውን በቅርስነት የተቀመጠውን ልበ ኩሩነታቸውን አውጥተው ሰውት፡፡ ሊመፀወቱ፤ እርዳታ ሊጠይቁ ወሰኑ፡፡ ሊያውም ከቀድሞ ስራ ባልደረባቸው፡፡

እግራቸውን እየጎተቱ፤ ሰውነታቸው እየተሸማቀቀ፤ ነፍሳቸው የፅልመት ካባዋን ተከናንባ ከደቂቃዎች በኋላ ከቀድሞው መስርያ ቤታቸው ደጅ ላይ ደረሱ፡፡ ቀና ብለው ህንፃውን ተመለከቱ፡፡ ባለ ሶስት ፎቅ ህንፃ ዛሬም ከነግርማ ሞገሱ እንደተገተረ ነው፡፡

በእርጋታ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ እግራቸውን ባነሱበት ቅፅበት የቀድሞ የስራ ጓደኞቻቸው በግቢው ውስጥ ሲንቀሳቀሱ አዩና ልባቸው ትር ትር ብሎ ቆሙ …ቆሙ…አልተንቀሳቀሱም …ደቂቃዎች ተቆጠሩ፡፡ በቆሙበት አፍታ አመታትን አጠነጠኑት ወደኋላ፡፡ ሃያ አምስት ፣ሃያ፣ ዓስራ አምስት ፣ ዓስርና ዓምስት ዓመታት …

ምንጭ፡- ይታገሱ ጌትነት፣2007ዓ.ም፣ ከገጽ 73-76/፣የደመና መንገድ አጫጭር ልቦለዶች ስብስብ፣ ላይ የተወሰደ ፡፡

1. ከላይ የቀረበው ምንባብ ተፅፎ የቀረበው በምን ያክል አንቀፅ ነው?

    ሀ.በሁለት　　　　ለ.በሶስት

    ሐ.በአራት　　　　መ.በአምስት

2. በአንቀፅ አንድ ላይ ፀሀፊው ‹‹**የሞት ለሆሳስ** ››ሲል ማለቱ ነው?

    ሀ.የባለታሪኩን ጥንካሬ　　　　ለ. የባለታሪኩን መድከም ሲገልፅ

    ሐ.የባለታሪኩን ለውጥ ሲገልፅ　　　　መ.የባለታሪኩን መበርታት ሲገልፅ



LIVEWORKSHEETS

3. እህል **<u>በአፋቸው ላይ ከዞረ</u>** ዛሬ ሶስተኛ ቀናቸው ነው፡፡ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ሀረግ ሀሳቡ ------ነው፡፡

ሀ.ምግብ ከበሉ ለ. ምግብ ካዩ

ሐ.ምግብ ከሰሩ መ.ምግብ በአካባቢያቸው ከዞረ

4. እድሜ ልካቸውን በቅርስነቱ የተቀመጠውን ልበ ኩሩነታቸውን አውጥተው **<u>ሰውት፡፡</u>** የተሰመረበት ቃል ፍቺ -------ነው፡፡

ሀ.ገደሉት ለ. ተጠቀሙት

ሐ.አቆሙት መ.ሰበሰቡት

5. ከዚህ ምንባብ (ጹሁፍ )የምንማረው ምንድን ነው ?

ሀ.ጉልበት ሲደክም ሃብት እንደሚመጣ ለ.ጉልበት ሲደክም ረዳት እንደማያስፈልግ

ሐ.ሽማግሌዎችን (ሀረጋውያን) ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው መ. የእርጅናን መልካምነት

6. የቀድሞው ትዝት የተገለጸው በፁሁፉ ውስጥ በስንተኛው አንቀፅ ነው?

ሀ.በአንቀፅ አንድ ለ.በአንቀፅ ሶስት

ሐ.በአንቀፅ አምስት መ. በአንቀፅ አራት

7.በመጀመሪያው አንቀፅ ማለትም ‹‹...ልባቸው ትርትር ብሎ ቆሙ...ቆሙ... አልተንቀሳቀሱም ...ደቂቃዎች ተቆጠሩ፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው ስርአተ ነጥብ የሚገልፀው ----ነው፡፡

ሀ.የሃሳብ ማለቅን ለ.የሀሳብ (የድርጊት )መቀጠልን

ሐ. በስህተት የገባ ነው መ.የሚገልፀው ነገር የለም



LIVEWORKSHEETS

**መመሪያ ሁለት**፡-ከተራ ቁጥር 8-40 ድረስ የተለያየ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። እያንዳንዱን ጥያቄ በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ (ምረጪ)።

8. የለሆሳስ ንባብ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ድምፅን ከፍ በማድርግ ማንበብ ለ. ለሌላ ሰው ማንበብ

ሐ. ድምፅ ሳያሰሙ በእዝነ ህሊና ማንበብ መ. በቡድን ማንበብ

9. ከቀረቡት ስሞች መካከል የተፀውኦ ስም የሆነው የቱ ነው?

ሀ.ሀገር ለ.ትምህርት ቤት

ሐ.መንገድ መ. ሚኒሊክ ትምህርት ቤት

10. ስለአንቀፅ አፃፃፍ ትክክል ያልሆነው ሀሳብ የቱ ነው?

ሀ.ተያያዥነት የሌላቸው ዓረፍ ነገሮች መጠቀም ለ. ስለአንድ ሀስብ የሚገልፅ ማድረግ

ሐ. መልክቱን ብስለት ያለው ማድረግ መ. ዋና አረፍተ ነገር ማስቀመጥ

11. "**መንገደኞቻችን**" የሚለው ቃል በምዕላዳዊ አፃፃፍ ተነጣጥሎ ሲፃፍ፡-

ሀ .መንገድ -ኞ-ቻችን ለ.መንገድ -ኧኛ - ኦች - ኣችን

ሐ.መንገደኛ -ኦቻችን መ. መንገድ -ኛ ኦች-ኣች-ን

12. ጎበዙ ተማሪ በፍጥነት መጣ። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ተውሳከ ግሳዊ ቃሉ

የትኛው ቃል ነው?

ሀ.ጎበዙ ለ.በፍጥነት

ሐ. መጣ መ. ተማሪ

13. ሽማግሌው በገንዘብ **መረዳት** ይፈልጋል። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ------ነው።

ሀ . መገንዘብ ለ.መስጠት

ሐ. መደገፍ መ.ማከፋፈል



LIVEWORKSHEETS

14. ከቀረቡት ምርጫዎች ውስጥ የማዳመጥ ክህሎት የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ.ማስታወሻ አለመጠቀም ለ.ያለአላማ ማዳመጥ

ሐ. ዋና መልእክት አለመለየት መ. በትኩረት ማዳመጥ

15. --------የምንለው በአንድ አንቀጽ ውስጥ ዋናውን ሃሳብ አጠቃሎ የሚይዝልንና በአንቀፅ ውስጥ የሚገኝ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡

ሀ . ሀይለ ቃል ለ.ዋና ዓረፍተ ነገር

ሐ.መዘርዝራዊ ዓረፍተ ነገር መ.ሀናለ መልስ ናቸው

16. ከቀረቡት ስሞች መካከል በብዙ ቁጥር የተገለፀው ስም የትኛው ነው?

ሀ.መምህር ለ.ቃላት

ሐ. ጽፈት ቤት መ. ዓረፍተ ነገር

17. ከሚከተሉት ቃላት ወይም ሀረጋት ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃል ወይም ሀረግ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በመሆኑም ለ. ከፍተኛ

ሐ. አሰራር መ. ተሰርቷል

18. ተማሪዎች ማንበብ <u>ይወዳሉ</u>፡፡ የተሰመረበት ቃል የዓ.ነገር መዋቅሩ ----ነው፡፡

ሀ.ስም ለ.ግስ

ሐ.ተሳቢ መ.ባለቤት

19. "ቋንቋ የሰው ልጅ ትልቁ መሳሪያ ነው፡፡ ባህሪውም ዘፈቀዳዊነት፣ ምልዑነት ወዘተ ያለው ነው፡፡ ጠቀሜታውም የሰውልጅ ሀሳቡንና ስሜቱን ለመግለፅና ለማስተላለፍ ይጠቀምበታል ፡፡"... ይህ ቅንጭብ ፁሁፍ በአይነት ከየትኛው የፁሁፍ አይነት ይመደባል?

ሀ.አመዛዛኝ ፁሁፍ ለ. ተራኪ ፁሁፍ

ሐ.ገላጭ ፁኑፍ መ.ስዕላዊ ፁሁፍ



LIVEWORKSHEETS

20. ከቀረቡት ርዕሶች መካከል ለማወዳደርና ለማነፃፀር ስልት ርዕስ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ . የሀገርና የእናት አንድነትና ልዩነት ለ. የሀገር ጠቀሜታንና ጉዳት

ሐ. ከገንዘብና ከዕውቀት የሚበልጠው መ. የጤናና የሰላም አስፈላጊነት

21. ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ተሸጋሪ ግስ ያልሆነው -----ነው፡፡

ሀ .ተኛ ለ.ሰራ

ሐ. አነበበ መ. ሰበረ

22. ከሚከተሉት ውስጥ ለውስብስብ ቃል ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ቃል ወይም ሀረግ የትኛው ነው?

ሀ .ስልት ለ.እንደየአነጋገራቸው

ሐ. መንገድ መ. ባህሪ

23. የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ከወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ የሚለየው ይዘት ወይም ነጥብ የቱ ነው?

ሀ . ቀን ለ. የላኪ ስም

ሐ.የተቀባይ አድራሻ መ. ቁጥር

24. ፈተና **<u>እየተፈተነ ነው</u>**፡፡ የተሰመረበት ግስ የሚገልፀው የምን ጊዜ አይነትን ነው?

ሀ. የትንቢት ጊዜ ለ.የኃላፊ ጊዜ

ሐ. የወደፊት ጊዜ መ. የአሁን ጊዜ

25. ከሚከተሉት ውስጥ የስነ ቃል አይነት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ . ተረት ለ. እንቆቅልሽ

ሐ.ግጥም መ.እንካስላትያ

26. አዳምጦ የቀረበውን ምንባብ ወይም ያዳመጠውን ነገር መልእክት ለመረዳት መደረግ ያለበት ተግባር የቱ ነው?

ሀ .እያቆራረጡ ማዳመጥ ለ. ትኩረት በመስጠት ፍሬ ሀሳቡ ላይ ማተኮር

ሐ. በመጀመሪያ የቀረበውን ብቻ ማዳመጥ መ. ያለዝግጅት ማዳመጥ



LIVEWORKSHEETS

27. ለሰው ልጅ ህይወት መቀጠል **እፅዋት** ያስፈልጋሉ። የተሰመረበት ቃል ምን አይነት ስም ነው?

ሀ . ተፀውዖ ስም ለ. የረቂቅ ስም

ሐ.የቃል ክፍሉ ስም አይደለም መ. የወል ስም

28. አንድ ሰው ጥሩ አንባቢ ነው የሚባለው ምንምን ነገሮችን በአግባቡ ማድረግ ሲችል ነው ?

ሀ.ቃላትን፣ሀረግትንና ዓ.ነገሮችን በተገቢው ንበት ሲያነብ ለ. የፁሁፉን ፍሬ ሀሳብ ሲለይ

ሐ ፊደላትን እየነጣጠለ ሲያነብ መ. ሀና ለ መልስ ናቸው

29. "**መሰሪ**" የሚለው ቃል ትርጉሙ ------ነው።

ሀ. ሞኝ ለ. ደፋር

ሐ. ነገር የሚፈጥር መ. ብርቱ

30. ከቀረቡት ውስጥ ቅጥያ የተጨመረበት ቃል የትኛው ነው?

ሀ .ስር ለ. ቤት

ሐ. ህይወት መ.ስለተማሪ

31. ከሚከተሉት ውስጥ **ሰነፍ** ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ፡-

ሀ . ብርቱ ለ.አመለኛ

ሐ. ግልፍተኛ መ.ልግመኛ

32. ትክክለኛ ስርዐተ ነጥብ የተጠቀመው አረፍተ ነገር የቱ ነው?

ሀ. ያለ ዝግጅት (ፈተና) መፈተን ያስቸጋራል። ለ.ፈተና በመረዳት (በመገንዘብ) ይመለሳል።

ሐ.(ፈተና) አቅምን ይፈትሻል ። መ. ፈተና ሲቀርብ ማንበብ (ጥሩ) ነው ።

33. የቃላዊ ግጥም ጠቀሜታ ሊሆን የሚችለው ፡-

ሀ . የሰው ልጅ ታሪክ ሲጠና እንደምንጭነት ያገለግላል። ለ. ያዝናናሉ

ሐ. መልካም ስነምግባር ተጠብቆ እንዲቆይ ያግዛል። መ. ሁሉም



LIVEWORKSHEETS

34. -------የድርሰት አይነት ሲሆን የሚለይበትን ፣የሚመረጥበትንና የሚልቅበትን

የሚያሳይ ሆኖ አላማውም የአንባቢን ሀሳብ ማስቀየር ወይም ማሳመን ነው።

ሀ. አመዛዛኝ ድርሰት ለ. ገላጭ ድርሰት

ሐ.ታሪካዊ ድርሰት መ. ስዕላዊ ድርሰት

35. **በዚህ ወር የሞዴል ፈተና እንፈተናለን**። ድርጊቱ የሚያመለክተው የምን ጊዜ ነው?

ሀ . የሀላፊ ጊዜ ለ.የአሁን ጊዜ

ሐ.የትንቢት ጊዜ መ.የሀላፊ ቅርብ ጊዜ

36. ተንኘው ክፉኛ ታሟል። በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ተውሳከ ግሳዊ ቃሉ

የትኛው ነው?

ሀ . ታሟል ለ.ክፉኛ

ሐ. ተንኘው መ. ተንኘው ክፉኛ

37. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የግዜ ተውሳከ ግስ ያለው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ .ጥንት መልካም ነበር። ለ. መሄድ አለብኝ።

ሐ. ደከመኝ አረፍኩ ። መ.ማንበብ ያስፈልገኛል ።

38. "ማረስ ጥሩ ነው አቧራ እስኪነሳ

ሆድ ባዶ አይሆንም ብርድ ሲነሳ።"የሚለው ቃላዊ ግጥም ምን አይነት ቃላዊ ግጥም ነው?

ሀ .የሙሾ ለ. የስራ

ሐ.የዓውዳመት መ. የልጆች ጨዋታ

39."**ስመጥር**" ለሚለው ቃል አቻ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ፦

ሀ .ታዋቂ ለ.ምሁር

ሐ.አታላይ መ. የቀለም ቀንድ

40."**ሰናይ**" ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ቃል የትኛው ነው?

ሀ . ጥሩ ለ. መልካም

ሐ. መጥፎ መ. ሀሴት



LIVEWORKSHEETS

LIVEWORKSHEETS